ሕገ-መንግስት እውቅና የተሳጣቸው እና በማንኛውም ሁኔታ የማይገደቡ መብቶች ተገቢው ጥበቃ እንዲያደረግላቸው፤ የፀጥታ ኃይሎች አላስፈላጊ እና ተመጣጣኝ ያልሆነ ሃይል ከመጠቀም እንዲቆጠቡ፤

5. የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የሰብዓዊ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ዜጎች ድጋፍ በማቅረብ እንዲረባረቡ፤ በሀገራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሽፋናቸው እየጨመረ እና መጠነ ሰፊ ጉዳት እያደረሱ የሚገኙ ግጭቶች እንዲያበቁና ዘለቄታዊ መፍትሄ እንዲፈለግላቸው ከመቼውም ጊዜ በላይ ትኩረት በመስጠት ርብርብ እንዲያደረጉ፤

6. የሚዲያ ተቋማት፣ የማህበረሰብ አንቂዎች፣ እና የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች፤ በሃላፊነት እንዲንቀሳቀሱና ግጭቱን ከሚያባብሱ ድርጊቶች እንዲቆጠቡ እንዲሁም ግጭቶች በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ ጥሪ እያቀረብን፤

በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በሀገራችን ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን፤ የሚፈጠሩ ግጭቶች እና አለመግባባቶች ሁሉ በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኙ የጀመረውን ሁለንተናዊ ጥረት አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን ለማረጋገጥ ይወዳል ።

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት
ECSOC
ETHIOPIAN CIVIL SOCIETY ORGANIZATIONS COUNCIL

<u>*ስለ የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት*</u>

*የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ምክር ቤት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 በአንቀጽ 85 መሰረት የተቋቋመ ገለልተኛ ተቋም ሲሆን የሲቪል ማህበረሰብ ዘርፉን በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲንቀሳቀስ በአዋጁ ኃላፊነት ተሰጥቶታል። በአሁኑ ወቅትም ከ4600 በላይ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች የምክር ቤቱ አባላት ናቸው።*

Scanned with CamScanner